# «የኛ ሰው»

ቋንቋን ያከብራሉ። ቃላትን ይንከባከባሉ። ለሥነ ጽሑፋዊ ውበት ይጠነቀቃሉ። የአጻጻፍ ስልታቸው ያስደስታል። ስለሆነም የእውነተኛ ታሪክም ሆነ የልብወለድ መጽሐፎቻቸው የአንባቢን ሙሉ ትኩረት ይስባሉ። ከሌላ ቋንቋ የተረጎሟቸውንም ሥራዎቻቸውን በጥንቃቄ መርጠውና በውብ አማርኛ አሳምረው የማቅረብ ስጦታቸውን ደጋግመው አስመስክረውባቸዋል። በአጭር አገላለጽ ሰውዬው የጽሑፍን ክቡርነት ጠንቅቀው ያወቁና ከሙሉ የሃላፊነት ስሜት ጋር ግዴታቸውን የተወጡ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ጸሐፊ ነበሩ። ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ያከበሩ የብዕር ሰው . . . «የኛ ሰው»።

ወቅቱን በትክክል ባላስታውሰውም የአምስተኛ ወይም የስድስተኛ ክፍል ተማሪ ከነበርኩባቸው ጊዜያት ጀምሮ ነበር የደራሲ ማሞ ውድነህን ሥራዎች ማንበብና ማድነቅ የጀመርኩት። በጊዜው ርዝመት የተነሣ በትክክል ትዝ ባይሉኝም ደራሲው ለሕትመት ያበቋቸውን አብዛኛዎቹን መጻሕፍት አንብቤአለሁ። ያን ጊዜ ለደራሲው የነበረኝ አድናቆትም አሁንም አብሮኝ አለ። በነዚያ ድንቅ ለጋ የመማሪያ ዓመታት እንደ አቶ ማሞ ውድነህ አይነቶቹ የአገራችን ጸሐፊያንና ገጣሚያን ያቀርቡልን የነበረው የንባብ ድግስ የሚጠገብ አልነበረም። ታዲያ በዚያ የልጅነት ወቅት የመጽሐፍ ፍቅር ከነበራቸው ጥቂት አብሮ አደግ ጓደኞቼ ጋር ሆነን «የኛ ሰው» የሚል ቅጽል ስም አውጥተንላቸው በዚያ ስያሜ ነበር አቶ ማሞን የምንጠራቸው —ካሳተሟቸው መጻሕፍት አንዱ ከሆነው «የኛ ሰው በደማስቆ» ስያሜውን በመውሰድ። እውነትም «የኛ ሰው»!

ያወጣንላቸው ቅጽል ስም በወቅቱ ለእኛ ትልቅ ትርጉም ነበረው። የአቶ ማሞ መጻሕፍት እኛን የዚያን ጊዜውን ታዳጊ ወጣቶች ወቅታዊ ከሆኑ ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ጋር አስተዋውቀውናል ለማለት ይቻላል። ምናልባት በወቅቱ ባንገነዘበውም ስለ«ጂኦፖሊቲክስ» ምንነት መግቢያ የሆኑንን ጠቃሚ ነጥቦች ከአቶ ማሞ መጻሕፍት አግኝተናል ብዬ አስባለሁ። ስለመካከለኛው ምሥራቅ ግጭቶችም ሆነ አገራትን ወደ ጦርነት ስለሚያስገቡ ፖለቲካዊ ጉዳዮች በአቶ ማሞ መጻሕፍት በኩል የአቅማችንን ያህል ግንዛቤ ማግኘታችንም አልቀረም። ከጓደኞቼ ጋር በየመጻሕፍቱ ውስጥ ስለተካተቱት ታሪኮች እንወያይ የነበረው በታላቅ መገረምና በጋለ ስሜት ነበር። በየሣምንቱ መጨረሻ ላይ በአዲስ አበባ ሲኒማ ቤቶች እናያቸው እንደነበሩት ታዋቂ ፊልሞች ሁሉ የማሞ ውድነህ መጻሕፍትም በብዙ ያወያዩን ነበር።

የመጻሕፍቱ ስዕላዊነት በዚያን ጊዜ ከነበረን ንጹሕ የማወቅ ፍላጐትና ሩቅ ተጓዥ ዐይነ ኅሊና ጋር ተዳምሮ እጅግ ልዩ የሆነ ደስታ ይሰጠን እንደነበር አስታውሳለሁ። ከመጽሐፍ ብቻ ሊገኝ የሚችል እውነተኛ ደስታ! «ዘጠና ደቂቃ በኢንቴቤ»ን ከነሄርኩሊስ አውሮፕላኑ፤ «የኦዴሣ ማኅደር»ን ከባለጀግኑ ፒተር ሚለር ጋር . . . ሌሎቹንም መጻሕፍት እንዲሁ ከየገጸባሕርያቱ ጋር እያነሣን፥ የራሳችንን ግምትና ትንተናም እየጨመርን ታሪኮቹን ማብራራት አንዱ

የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያችን ነበር። እውነትም ለመደበኛ ትምሕርት የምናጠናቸውን ኰስታራ መጻሕፍት ከሚያጣፍጡልን ኢትዮጵያውያን ደራስያንና ገጣሚያን መካከል «የኛ ሰው» አንዱ ነበሩ። የማሞ ውድነህ ሥራዎች የሌሎች ደራስያንንም መጻሕፍት እንድንመለከት ምክንያት እንደሆኑን መግለጽ ተገቢ ይሆናል። በተለይም ደግሞ በታሪካዊ ልብወለድ የአጻጻፍ ዘይቤ የተካኑትን የዘመኑን ደራስያን እንድናውቅ «የኛ ሰው» መንገድ ከፍተውልናል ማለት ይቻላል። ለአብነት ያህል «የኦዴሣ ማኅደር» ከፍተኛ አድናቆትን ካተረፈው እንግሊዛዊ የልብወለድ ደራሲ ከፍሬድሪክ ፎርሳይዝ ሥራዎች ጋር እንዳገናኘን መግለጹ በቂ ይመስለኛል።

ከጥቂት ዓመታት በፊት አቶ ማሞ ሲታከሙበት ወደነበረው የዋሽንግተን ዲሲ ሆስፒታል ከአንድ ወዳጄ ጋር ሄደን ጠይቀናቸው ነበር። ከተኙበት የሆስፒታል አልጋ ላይ ሆነው ረጋ ባለ መንፈስ አንዳንድ ቁምነገሮችን ቢያጫውቱንም ለእኔ ከፍተኛ ደስታ የሰጠኝ ምስጋናዬንና አድናቆቴን በአካል ልገልጽላቸው መቻሌ ነበር። በእርግጥ የማሞ ውድነህን መጻሕፍት ካነበብኩ ብዙ ዓመታት ተቆጥረዋል። ዜና እረፍታቸውን ስሰማ ለጊዜው ኃዘን ቢሰማኝም በሥራዎቻቸው በኩል ለእኔና ለጓደኞቼ የተዉልን ጣፋጭ ትዝታ ግን ወዲያውኑ ፈገግ እንዳሰባለኝ አልሸሽግም። የሥነ ጽሑፍ ሥራዎቻቸውን የሚያውቁ ሁሉ ይህን ስሜቴን ይጋራሉ ብዬ አስባለሁ። ማሞ ውድነህ ለአገራቸው ያበረከቱት ከፍተኛ አስተዋጽዖም ለቤተሰቦቻቸውም ሆነ ለኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ጥሩ መጽናኛና ዘላቂ ማስታወሻ እንደሚሆን አምናለሁ።

«የኛ ሰው» . . . በራሴና በጓደኞቼ ስም የማቀርብልዎ ምስጋና ከልብ ነው። እግዚአብሔር ይስጥልን።

---

ቴዎድሮስ አበበ
የካቲት ፳፯ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም. | March 6, 2012